# የኢትዮጵያ ጊዜ ግንዛቤና ዘመናዊነት

መሳይ ከበደ

ፈላስፎችን የሚያስማማ አንድ ነገር ቢኖር የጊዜ ምንነት የፍልስፍና አምብርት ጥያቄ መሆኑ ነው። ምዕራባዊውን ዓለም እንደ ምሳሌ ብንወስድ፤ ስለ ጊዜ ሳይመራመር የቀረ ታዋቂ ምዕራባዊ ፈልስፋ የለም። የጀርመኑ ፈላስፋ፤ ማርቲን ሃይደገር፤ የጊዜ ጥያቄን አንብርትነት ሲያመለክት፤ "ጊዜ ተብራርቶ የኑባሬ ማንኛውም ግንዛቤና ትርጓሜ አድማስ መሆኑ በትክክል መታወቅ አለበት" ብሏል።[1] እንዲሁም በፈረንሳዊው ፈላስፋ ሃንሪ በርግሶን አባባል፤ የፍልስፍና ጥያቄዎች አስቸጋሪ የሆኑበት ዋናው ምክንያት "ዕውኑን ጊዜ ስለማናስብ" ነው።[2] የጊዜ ጥያቄ በጣም ግራ አጋቢ በመሆኑም ነው አንዳንድ ፈላስፎች ጊዜ ዕውን ያልሆነ የውሸት ዕይታ ነው ያሉት። ለምሳሌ ፓርመኒዲዝ የተባለው የጥንታዊ ግሪክ ፈላስፋ ኑባሬን ከጊዜ ውጪ ማሰብ እንዳለብን ሲያስርዳ፤ "ቀድሞ ወይም ወደፊት አይኖርም፤ ሁሌም በአንድነት ሙቼም ሳይቋርጥ ያለ ነውና" ሲል ተናግሯል።[3]

የዚህ ፅሑፍ ዋና ዓላማ አስቸጋሪ የሆነውን የጊዜ ጽንሰሐሳብ ኢትዮጵያውያን[4] እንዴት ይመለከቱትል የሚል ነው። ጊዜ የፍልስፍና ወሳኝ ጥያቄ በመሆኑም አመለካከቱን መመርመር የኢትዮጵያ የዓለም አመለካከትን ሥር መሰረት ያስጨብጣል። በተለይም የጊዜ ግንዛቤ ከታሪካዊ አስተሳሰብ ጋር የተሳሰረ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን ምንነታቸውንና ዓላማቸውን እንዴት አደተረጎሙ ያመለከታል። በያዙት ዓላማ አንጻርም እንዴት ዘመናዊነትን እንደተቀበሉት ይጠቁማል። የአቀባበሉ ሁኔታ ደግሞ ለምን ዘመናዊነትን በኢትዮጵያ ለማስፈን እንዳልተቻላቸው አብሮ ይናገር።

## ጊዜና ኑባሬ

ጊዜን ዋናና አስቸጋሪ ጥያቄ የሚያደርጉትን ምክንያቶች በአጭሩ እንመልከት። ስለ መኖር በተመራመርን ቁጥር ምርምሩ ጊዜ ምን ማለት ነው? ወደሚል ጥያቄ በቀጥታ ይቀየራል። ኑሮ መጀመሪያና መጨረሻ ያለውና በተለያዩ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች የሚያልፍ ክስተት ነው። ተፈጥሮ የሆነ ሁሉ መጀመሪያ እንዳለው ሁሉ መጨረሻውም አይቀሬ ነው። እንዲሁም የሚኖር ነገር

# The Ethiopian Conception of Time and Modernity

**Messay Kebede**, *University of Dayton*
Translated by Bethlehem Hailu Dejene, *Northwestern University*

If there is one thing that philosophers agree upon, it is that the meaning of time is a central philosophical question. If we take the Western world as an example, there is no famous philosopher who has not investigated time. The German philosopher Martin Heidegger, to indicate the centrality of time, writes: "The central problematic of all ontology is rooted in the phenomenon of time correctly viewed and correctly explained."[1] Likewise, according to the French philosopher Henri Bergson, the main reason that philosophical questions are difficult is because "we do not think real time."[2] The fact that the question of time is very confusing has led some philosophers to claim that time is an unreal, illusory notion. For example, the ancient Greek philosopher known as Parmenides, in order to explain that we have to think of being as outside of time, says that "it is neither was nor will be, it simply is—now, altogether, one, continuous."[3]

The main intention of this essay is to ask how Ethiopians perceive this difficult notion of time.[4] Because time is a decisive question for philosophy, to examine how it is perceived allows us to understand how Ethiopians have seen the world. Particularly, as the conception of time is tied up with historical thinking, it can show us how Ethiopians have interpreted their identity and their goals. The goals they espouse indicate how they have received modernity. In return, how they received modernity should inform us about why it has been so impossible to modernize Ethiopia.

## BEING AND TIME

Let us look briefly at the reasons for the importance and difficulty of the question of time. Whenever we seek to study life, our inquiry leads us directly to the question: "What is the meaning of life?" Life is a phenomenon that has a beginning and end but which also passes through various changing situations. As everything that is natural has a beginning, it is natural that it has an end. Furthermore, since everything that lives experiences growth, it goes through

ሁሉ በእድገት ሁኔታ ውስጥ ስለሚያልፍ የማያቋርጥ መለዋወጥን ያሳያል። የመኖር ባሕርያት የሆኑት የመጀመር፣ የማደግ፣ የማርጀት፣ የማለቅ ሁኔታዎች ሁሉ የጊዜ መግለጫዎች ናቸው።

እዚህ ላይ የሚነሳ አስቸጋሪ ነጥብ አለ። አንድ ነገር ሲለዋወጥ ምንነቱን ያጣል ካልን ሥለ ነገሩ የምንሰጠው ብያኔ ትክክለኛነት አይኖረውም። ምክንቱም ነገሩ ቋሚ ባህርይ ስለሌለው በተለዋወጠ ቁጥር ብያኔያችንን ይሽረዋል። መለዋወጥ የሚያስከትለው ዓለም በሰው ልጅ አእምሮ ሊታወቅ አይችልም የሚል ድምዳሜ ይሆናል ማለት ነው። በተጨማሪም፣ ሳያቋርጥ የሚለዋወጥ ነገር አለ ማለት ፍች የሚሰጥ አነጋገር አይመስልም። አሁን ያለው ሲለወጥ፣ መኖሩ የት ይገባል፣ ምን ሆነ ይባላል? ባዶ ሆነ የምንል ከሆነ፣ ባዶ የሌለ ነገር ስለሆነ እንዴት ያለው ወደ ምንም ይቀየራል? በመሆኑም አለ መባልና ጊዜ አብረው የሚሄዱ አይመስሉም።

የለም፣ ነገሩ ሲለወጥ ባህሪው አይቀየርም የምንል ከሆነ ደግሞ፣ ጊዜ እውነታ የሌለው ክስተት ይሆናል። ነገሩ ካልተለወጠ በጊዜ ውስጥ ማለፉ ያመጣው ድርጊት የለም ማለት ነውና። በመሆኑም የምናየው መንቀሳቀስና መለዋወጥ የቁም ቅዠት ይሆናል።

ከዚህም ችግር አልፈን በመሄድ መኖርን በትክክልና በተሟላ መልኩ ለማሰብ ስንሞክር ከዘለዓለማዊንትና ከለውጠቢስነት ጋር ይዛመድብናል። ኑሮ ፍጹም የሚሆነው መጀመሪያና መጨርሻ ሳይኖረው፣ ከማደግና ከመለዋወጥ የጸዳ ባሕርይ ሲያሳይ አይደለምን? ተፈጥሮ ተፈጣሪ እንደ መሆኑ፣ እሱን ሊፈጥር የሚችለው ኃይል እራሱ ከጊዜ የወጣ መሆን አይኖርበትምን? ስለዚህ ነው ፍጹም መኖርን እግዚአብሔር የምንለውና ዋና ባሕሪውንም ከጊዜ ሂደት ውጪ የምናድርገው።

የመኖር የማይጣጣሙ ባሕርያትን ለማስታረቅ ስንነሳ ጊዜን እንደ ሂደት ወይም ጉዞ እናስባለን። መጀመሪያ ያለውና ተለዋዋጭ የሆነ ኑሮ የሚያከናውነው ግብ ወይም ዓላማ ስላለው በጊዜ ውስጥ ይጓዛል። ይህ አባባል አንድ የሐሳብ አቅጣጫ ይከፍታል። የመለዋወጥ ምስጢር ዓላማን ማስፈጸም ከሆነ፣ አንዱ ዓላማ ወደ ላቀ የመኖር ደረጃ መሸጋገር ሊሆን ይችላል። የዓላማው መከናወንም ወደ መኖር ፍጹም ደረጃ ሊያሸጋግር ይችላል። በሌላ አባባል፣ የጊዜ ምስጢር ዘለዓለማዊነት ይሆናል ማለት ነው።

የጊዜ ጥያቄ ከመኖር ጋር የተሳሰረው የመኖርን ፍች ወይም ምስጢር ገላጭ በመሆኑ ነው። ሃይደገር እንዳለው፣ የጊዜን ጥያቄ ማብራራት የመኖርን ምስጢር መፍታት ነው። ለዚህም ነው ሰዎች ጊዜ ግብ አለው ለማለት የበቁት። ጊዜ ግብ ሲኖረው ሂደት ይሆናል፣ ሂደቱም የኑሮን ግብ ያስፈጽማል። ለምሳሌ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ሁሉ የጊዜ ሂደት ዘለዓለማዊንት ያዘጋጃል ይላሉ።

## የኢትዮጵያ ሁኔታ

የኢትዮጵያ የጊዜ ግንዛቤን የምንጨብጠው ጊዜ የኑሮን ትርጉም አብሳሪ መሆኑን ስንቀበል ነው። ግንዛቤውንም ማመንጨት ያለብን ከነበሩበት ሁኔታ በመነሳት እንዴት ኢትዮጵያውያን የመኖራቸውን ፍች ቀመሩ ብለን በመጠየቅ ነው። ከነበሩበት ሁኔታ ካልተነሳን የምናገኘው ውጤት ከመኖር ፍች ምርመራ ጋር የተገናኘ አይሆንም። እንዲሁ ብቅ ያለ ሐሳብ ነው ከማለት በስተቀር ኑሮንና ጊዜን በጥምር መመልከት አያስችለንም።



uninterrupted change. The processes of beginning, growing, aging, and ending, which are the characteristics of life, are thus expressions of time.

There is a difficult point that needs to be raised here. If we say that when something changes, it loses its essence, our judgments about this thing will be incorrect. Since it has no permanent characteristics, our judgments are falsified each time the thing changes. Continuous change leads, therefore, to the conclusion that the world cannot be known by the human mind. Furthermore, to say that continuous change is real does not seem to make sense. When what exists changes, where does its previous existence go—what can we say happened to it? If we say that it has become nothing, since nothing is nothing, how can something change into nothing? Accordingly, being and time do not seem to go together.

On the other hand, if we say that when a thing changes, its nature does not change, then time is a phenomenon without reality. For unless the thing itself changes, the fact that it has passed through time is without consequence. Therefore, the movement and the change that we see is nothing but an illusion.

Going further, when we attempt to think of life correctly and in its fullness, then it coincides with eternity and immutability. Does not life become absolute when it has neither beginning nor end and is free from the characteristics of growth and change? Since nature is created, does not the power that creates it have to be outside of time? This is why we say Absolute Life is God and why we place it outside temporality.

When we try to reconcile the incongruent characteristics of life, we think of time as a process and a journey. Living, which has a beginning and which involves change, has goals and aims and thus it passes through time. This approach opens a new direction of thought. If the secret of change is the accomplishment of goals, then one of the aims could be to accede to a higher level of life. The accomplishment of this aim could lead to life's absolute level. In other words, the secret of time is the state of eternity.

The question of time is tied to life because it reveals the meaning or secret of life. As Heidegger says, to dwell on the question of time is to unravel the secret of life. This is what makes people say time has a goal. When time has a goal, it becomes a process; this process accomplishes the goal of life. For example, adherents of Christianity and Islam say the process of time prepares us for the state of eternity.

## THE ETHIOPIAN SITUATION

We can grasp Ethiopia's understanding of time when we accept that time reveals the meaning of life. We must gain this understanding by examining how Ethiopians, starting from their situation, arrived at the meaning of life. If we do not start from their situation, our elucidation will not be connected with an inquiry into the meaning of life. It would fail to tie time to the meaning of life, thereby making the latter into a thought that just popped up.

We know that Ethiopia's situation turned the question of existence into a major concern. For a country that has existed as a lone island of Christianity for centuries, life inevitably holds a precarious character. In particular

የኢትዮጵያ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ መኖርን ጥያቄ ያደርግ እንደነበር እናውቃለን። ለብዙ ዘመናት ብቸኛ የክርስቲያን ደሴት ሆና ለተቀመጠች አገር መኖር አጠራጣሪ መልክ መያዙ አይቀርም። በተለይ በኃያላን እስልምና ተከታይ አገሮች መከበብና አልፎም የወረራ ጥረት መጋለጥ ለመኖር የሳሳ ጠባይ ሰጥቷል። ኑሮን የተረጋገጠ ለማድርግና አበረታታች ተስፋ ለመፍጠር ልዩ የታሪክ ግንዛቤ መቀመር አስፈላጊ ሆኗል። ይህም ታሪክ ለኢትዮጵያ ልዩ ተልዕኮ በመስጠት በድል አድራጊነት እስከመጨረሻ እንደምትቆይ ማረጋገጥ ይኖርበታል። የጊዜ ሂደት ተልዕኮውን መፈጸም ሲሆን የመኖር ፍችንም አብሮ ይሰጣል። የዚህ ድል አብሳሪ ታሪክ ግንዛቤ ዋና ምንጭ ክብረ ነገሥት የተባለው መጽሐፍ ነው።

እንደሚታወቀው ሁሉ የንግሥት አዜብና የንጉሥ ሰለሞን መገናኘት ሁለት ቁም ነገሮችን አስከትሏል። አንዱ የኢትዮጵያ ንጉሥ የሚሆነው የምንሊክ መወለድ ሲሆን ሁለተኛውና ዋነኛው ደግሞ የታቦት ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ መወሰድ ነው። የታቦቷን መወሰድ እንደተረዳ ንጉሥ ሰሎሞን በቀጥታ እንዲህ ብሏል፤ "የከበረችው የጽዮን ልጅ ክብር ተነስቷል። የጎስቋላዋ የኢትዮጵያ ልጅ ክብር ከፍ ብሏልና"።[5] ከፍተኛ ብስጭትና ሐዘን ውስጥም ንጉሥ ሰሎሞን በመውደቁ የትንቢት መንፈስ እንዲህ ሲል ጠይቆታል፤ "ይህ በእግዚአብሄር ፈቃድ ሆኗልና በአባትህ በዳዊት ዙፋን ላይ ለሚቀመጠው ለበኩር ልጅህ ነው እንጂ ለባእድ የተሰጠች አይደለችምና ለምን እንደዚህ ታዝናለህ?"[6] ይህ የክብረ ነገሥት አባባል በትክክል የሚያስቀምጠው እግዜር ኢትዮጵያን ለልዩ ዓላማ ማጨቱን ነው።

የኢትዮጵያ የጊዜ ግንዛቤ ለአገር ልዩ ዕጣ በመለገስ ብቻ አልተወሰነም፤ የግልሰቦችን ኑሮና ማህበራዊ ሥፍራንም ያጠቃልላል። የግለሰቦች ኑሮ በጣም ተለዋዋጭ፣ በብዙ ውጣ ውረዶችና አጋጣሚዎች የሚያልፍ እንደመሆኑ፤ ይህ ተቀያያሪ ሁኔታ ፍች የሚኖርው ወደ አንድ ግብ ሲጓዝ ብቻ ነው፡፡ የዚህ ግብ አፈጻጸም የጊዜ ሂደት ይሆናል። በተለይም፤ ጊዜ የሚራመደው በአንድ አቅጣጫ ወደፊት በመሄድ ነውን ለሚለው ጥያቄ ኢትዮጵያውያን የሰጡት መልስ የአመለካከታቸውን ፍሬ ነገር ይጠቁማል።

### የጊዜ ተፈራራቂነት

የኢትዮጵያ የጊዜ ግንዛቤ በትትክል እንዲገባን አንድ መሠረታዊ መነሻ መቀበል አለብን። እሱም እንደ ማንኛውም ቅድመ ዘመናዊ አመለካከት ኢትዮጵያውያን ጊዜን የተመለከቱት እንደ ተደጋጋሚ ክስተት ነው። ይህን ሐሳብ ሊሰጣቸው የቻለው በመጀመሪያ ደረጃ የተፈጥሮ ሁኔታ ነው። ተፈጥሯዊ ክስተቶች በሙሉ ይፈራረቃሉ። ቀን በማታ፤ ማታ በቀን ይተካል። ክረምት ሲያልፍ በጋ ይመጣል፤ በጋ ሲሄድ፤ ክረምት ይተካል። ሙቀት ወደ ቅዝቃዜ፤ ቅዝቃዜ ወደ ሙቀት ይሸጋገራል። ሕይወት ወደ ሞት፤ ሞት ወደ ሕይወት ይቀየራል።

ልክ እንደ ተፈጥሮ ግለሰባዊና ማህበራዊ ኑሮም የጊዜን ተፈራራቂነት ያረጋግጣል። ዛሬ የተደሰተ ነገ ያዝናል፤ ተመልሶም ይደሰታል። አባት ልጅ ሲወልድ፤ ልጅ ደግሞ አባት ይሆናል። ዛሬ የተነሳ ነገ በወደቀው ይተካል። ሀብታሙ ሲደኸይ ድሀ የነበረው ይከብራል። ንጉሥ ሲሞት ሌላ ንጉሥ ይመጣል።



the fact of being surrounded by powerful Islamic countries and exposed to attempts at invasion gave life a perilous meaning. To give life certainty and to conjure up encouraging hope, it became necessary to create a special understanding of history. By giving Ethiopia a special destiny, this history would confirm that Ethiopia will exist victoriously until the end. While the passage of time accomplishes this goal, it also provides the meaning of life. The main source of the understanding of this victory-proclaiming history is the book known as the *Kebra Negast.**

As is well known, the meeting of Queen Saba (Sheba) and King Solomon brought forth two important consequences. While one was the birth of Menelik who eventually became the king of Ethiopia, the second and more important outcome was the taking of the Ark of the Covenant to Ethiopia. When King Solomon discovered the disappearance of the Ark, he said directly: "The glory of the revered son of Zion has been removed, while the glory of the son of wretched Ethiopia has been raised."[5] Since King Solomon fell into deep disappointment and sadness, the spirit of prophecy asked him: "This hath happened by the will of God, and as the Ark has been given to your first son who sits on your father David's throne rather than a stranger, why are you so sad?"[6] This quote from the *Kebra Negast* shows precisely that God assigned Ethiopia a special role.

Ethiopia's understanding of time is not limited to assigning a special destiny to a country; it includes individuals' lives and social status. Since the life of the individual is constantly changing, since it passes through many highs and lows and incidents, this changing situation finds meaning only when it moves toward a goal. The accomplishment of this goal becomes the process of time. Above all, the answer that Ethiopians have given to the question of whether time moves forward and in one direction points to the essence of their outlook.

### CYCLICALITY OF TIME

To comprehend the Ethiopian conception of time correctly, we need to accept a basic point of departure. That is, like any premodern view, Ethiopians saw time as a repetitive occurrence. What enabled them to attain this idea, on the first level, was the condition of nature. All natural phenomena are cyclical. Day is substituted for night and night for day. When winter passes, summer arrives; when summer leaves, winter replaces it. The warm becomes cold, the cold warm. Life changes into death and death into life.

Like nature, individual and social life confirms the cyclicality of time. One who is happy today is saddened tomorrow, and goes back to being happy. When a father gives birth to a son, the son becomes a father. The one who has been promoted will be replaced tomorrow by the one who has been demoted. When the rich turns poor, the poor becomes rich. When a king dies, another king comes.

የኢትዮጵያ የጊዜ ግንዛቤ በትክክል የሚያንጸባርቀውን የከበደ ሚካኤልን አንድ ግጥም እንመልከት። የግጥሙ አርእስት "ሁሉም የሆነ ነው" የሚል ሲሆን፤ ከግጥሙ ውስጥ አለፍ አለፍ እያልን ብንጠቅስ የሚከተሉትን ሐሳቦች እናገኛለን።

ሰሎሞን ብሎናል ደኅ ተመልካች
አዲስ ነገር የለም ከፀሐይ በታች

ልበ ተላላ ሰው ዘላለም ይሞኛል
እስኪ ረግቶ ያለ ምን ነገር ይገኛል?
የተማመኑበት እየሆነ ፈራሽ
ሲፈጸም ይገኛል ያልታሰበው ጭራሽ
ደካማ ይጠናል ኀይለኛ ሲዋረድ
ቡቃያ ይለማል ያፈራው ሲታጨድ
ሰፊው ይቀንሳል ጠባቡ ሲሰፋ
ጨረቃ ታምራለች ፀሐይ ስትጠፋ
ሀብታሙ ሲደኸይ ድኻ ሰው ይከብራል
አንዱ ሲደፈርስ ሌላውም ይጠራል
ከእንቅልፉ ሲነቃ ቀድሞ የፈዘዘ
የሞቀው ይሄዳል እየቀዘቀዘ
ትንሹም ትልቅ ነው ትልቁም ትንሽ
መጥፎውም መልካም ነው መልካሙም ብላሽ
እንደ ሕልም ታይቶ ያልፋል እንደ ጥላ

የዚህ ዓለም ነገር ምንም የለው መላ
ተፈራራቂ ነው አዲስ ነገር የለም።[7]

ከዚህ ግጥም የምንረዳው መሠረታዊ አመለካከት ሁሉ ነገር የሚፈራረቅ በመሆኑ ምንም አዲስ ነገር የለም የሚል ነው። የሚታዩት ለውጦች ሁሉ የነበረውን፤ የታየውን የሚመልሱ እንጂ አዲስ ነገር የሚያመጡ አይደሉም። የጊዜ ተፈራራቂነት የሚያስከትለው ሌላ ዋና ሐሳብ ሁሉ ነገር ከንቱ እንደሆ ነው። ምንም ነገር ስለማይቆይ፤ ብሎም ወደ ተቃራኒው ስለሚለወጥ፤ ሁሉ ነገር አንጻራዊ ነው። በዚህ ዓለም ውስጥ ምንም ፍጹማዊ ነገር ስለሌለ ሕይወታችን አላፊና ተቀልባሽ ሁኔታዎችን በማሳደድ መወሰን የለበትም። በመሆኑም የጊዜ ተፈራራቂነትን የሚያጋልጠው ነገሮች እራሱን የቻለ ንባሬ እንደሌላቸው ብቻ ሳይሆን ወደ ተቃራኒዎቻቸው በመለወጣቸው እራሳቸውን የመምራት ችሎታ እደሌላቸው ጭምር ነው።

ይህም በመሆኑ እነዚህን ነገሮች ሁሉ መናቅና መሸሽ አለብን ማለት አይደልም። እንደ አመጣጣቸው በጸጋ መቀበል እንጂ፤ ምክንያቱም የጊዜ መፈራረቅ የሚያመለክተው የእግዜርን ፍጹም ኃይል ነው። እግዜር ይስጣል፤ መልሶም ይወስዳል። አንድን ሲሾም ሌላውን ይሽራል። አንድን ጌታ ሲያደርግ ሌላውን ያደኸያል። የነገሮች ቋሚነት ማጣትና ወደ ተቃራኒዎቻቸው መለወጥ የእግዜር መኖርንና የዓለም በእሱ ፈቃድ ብቻ መግዛትን ይጠቁማል። የነገሮች



Let us look at one of Kebede Mikael's poems, which correctly reflects Ethiopia's understanding of time. The title of the poem is "Everything Is Deja Vu." Here are some representative thoughts:

Solomon, the fine observer, told us
There is nothing new beneath the sun

The naive person is constantly fooled
Is there anything that stays the same?
While that which you have put your trust in crumbles
The unplanned is found happening
The weak becomes strong while the powerful is humiliated
Young plants grow while fruits are reaped
The wide shrinks, while the narrow expands
The moon becomes beautiful when the sun disappears
When the rich becomes poor, the poor becomes wealthy
When one thing becomes murky, another clears up
The one who was sleepy wakes up
The warm becomes colder
The small is big, the big small
The bad is good, the good bad
It appears like a dream and passes like a shadow
The nature of this world is unpredictable

In the past, in the future, and today in this world
There's nothing new; everything is cyclical[7]

The basic outlook we find in this poem is that, since everything is cyclical, there is nothing new. All the changes that are seen only replace what was previously seen; they do not bring anything new. The other important thought that is produced by the cyclicality of time is that everything is vain. Since nothing stays permanently and even changes into its opposite, everything is relative. Since there is nothing absolute in this world, our lives should not be limited to chasing transient and reversible conditions. Therefore, what the cyclicality of time exposes is not only that things do not have independent existence; the fact that things change into their own opposites also shows that they do not have the capacity to direct themselves.

Even so, we should not denigrate and avoid these things. Rather, we should accept them graciously as they come, because the cyclicality of time evinces the absolute power of God. God gives and takes back. While He appoints one, He demotes another. While He makes one a lord, He impoverishes another. The lack of permanence in things and their transformation into their opposites points to the existence of God and the fact that the world is ruled only by His will. The other lesson the cyclicality of things teaches us is not to be trapped by arrogance because we happen to be wealthy and

ተፈራራቂነት ሌላው የሚያስተምረን፣ በለጸግን፤ ሥልጣን ተቀዳጀን ብለን በትዕቢት ስሜት እንዳንጠመድ ነው። ትዕቢት ለራስና ለነገሮች አስመሳይ ነጻነት በመሥጠት የአምላክን ገዢነት የሚያድበሰብስ ዲበአካላዊ ውዥንብር ነው።

## ጊዜና እድል

እዚህ ላይ የኢትዮጵያን ልዩነት መመልከት ያሻል። ቅድመ ዘመናዊ አመለካከቶች ሁሉ ጊዜ ተፈራራቂ ነው ቢሉም አመለካከታቸው በአመዛኙ ያተኮረው ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ላይ ነበር። ኢትዮጵያውያን ግን ሐሳቡን ወደ ማህበራዊ ኑሮ በማዞር የጊዜ ተፈራራቂነት በሕብረተሰብ ውስጥም ይታያል ብለዋል። የግለሰቦች ማህበራዊ ሥፍራ ቋሚ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ይቀለባበሳልም እስከማለት ደርሰዋል። የከበደ ሚካኤል ግጥም እንደሚናገረው፤ ሀብታሙ በድሀው ይተካል፤ ደካማው ኃይለኛ ይሆናል። በቋሚ መደቦች በተከፋፈለ ማህበረሰብ ውስጥ ቋሚ ሥልጣንና ማህበራዊ ሥፍራ የለም ማለት የሚገርም አነጋገር ነው። የሰዎች ማህበራዊ ማዕረግ ይፈራረቃል ማለት በቋሚነት የሚያዝ ከፍተኛም ሆነ የበታች ሥፍራ የለም ማለት ነው።

አመለካከቱ በቀጥታ የሚያንጸባርቀው የኢትዮያን ማህበራዊ ግንዛቤ ነው። ቋሚ መደቦች አሉ፤ ነገር ግን ግለሰቦች በትውልድ የሚወርሱት ሥፍራ የለም። በተለይም ከፍተኛ ቦታዎች ከታች በሚመጡ ግለሰቦች ይነጠቃሉ። ይህ ከአንድ መደብ ወደ ሌላ መደብ የመሸጋገር ችሎታ ኢትዮጵያውያን ዕድል ብለውታል። ዕድል የሚገልጸው የኢትዮጵያን ማህበራዊ ኑሮ ተንቀሳቃሽነት ነው።

ከበታች ወደ በላይ ማህበራዊ ሥፍራ መሸጋገር ዕድገት እንደመሆኑ መጠን ዕድል ከማለት ይልቅ ለምን ኢትዮጵያውያን ችሎታ አላሉት ብለን ብንጠይቅ መልሱ ቀላል ነው። ችሎታውን የሚለግሰው እግዜር በመሆኑ በእርሱ መመረጥን ይጠይቃል። ከእግዜር የሚደርሰንን ለማሰብ የምንችለው እንደ ስጦታ ወይም ዕጣ እንጂ እንደሚገባን እስካልሆነ ድረስ ትክክለኛው አስተሳሰብ ዕድል የሚለው ነው።

የዕድል ጽንሰሐሳብ ከኢትዮጵያዊ ጊዜ ግንዛቤ ጋር የተቆራኘ መሆኑ ግልጽ ነው። የጊዜ መፈራረቅ ዕድል ከፋች ነው። የተለያዩና በበታችና በበላይ የተከፋፈሉ ማህበራዊ መቀመጫያዎች አሉ። ነገር ግን ግለሰቦች በተራ እንጂ በቋሚነት የሚይዟቸው አይደሉም። የፈረቃ ሕግ የወጣውን ስለሚያወርድ ግትር ማህበራዊ አቋም እንዳይኖር ያደርጋል። ስለሆነም በታች የነበረው ግልሰብ ከላይ ያለውን የሚተካበትን ሂደት ያመቻቻል።

ልክ እንደ አውሮፓ ቋሚ የመኳንንትና የንጉሥ ዘር ለመመስርት አለመቻሉ የኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ይመስክራል። በንጉሥ ብንጀምር፤ ሥልጣኑን በአራሱ ቤተሰብ ውሰጥ ለማስቀረት የቻለ የኢትዮጵያ ንጉሥ የለም። ይህ ማለት መቼም የንጉሥ ልጅ ሥልጣን አልወረሰም ማለት አይደለም። መንገሥ በዘር የወሰደው ልዩ መብት ሳይሆን ተቀናቃኞቹን ድል በማድረግ የተቀናጀው ሥልጣን ነው። ድሉም የሚያበሥረው ዕድሉን፤ ማለት በእግዜር የተመረጠ መሆኑን ነው። በዚህ የተነሳ በ ኢትዮጵያ እንድ ተዎድሮስ የተባለ የኮሶ ሻጭ ልጅ ሊነግሥ ችሏል።

ብዙ ጥናቶች እደሚያመለክቱት፤ እንደ አውሮፓ በገበሬውና በመኳንንቱ መካከል ግትር ልዩነት በኢትዮጵያ ውስጥ አልነበረም። ግለሰቦችን የሚለያቸው በዕድላቸው የተለያየ ስፍራ መያዛቸው እንጂ የትውልድ ዘራቸው አይደለም። ገበሬው በዕጣው ገባሪ ሆነ እንጂ የበታች ሰው አልነበርም። በመሆኑም ዕድሌ ተቀይሮ ያንዱን ከፍተኛ ቦታ አገኛለሁ እያለ ሳያቋርጥ ይመኛል።



powerful. By giving a false autonomy to the self and things, arrogance produces a metaphysical confusion by shrouding God's rulership.

## TIME AND FATE

At this juncture, it is necessary to point out Ethiopia's uniqueness. Even if all premodern views claimed that time is cyclical, such views mostly focused on natural phenomena. However, Ethiopians, by applying this thought to the social, have said that the cyclicality of time is seen in society too. Not only have they claimed that individuals' social place is not permanent, but they also have gone as far as to say it is subject to reversal. As Kebede Mikael's poem says, the wealthy is replaced by the poor; the weak becomes powerful. And when the rich becomes poor, the poor becomes wealthy. In a society that is divided into fixed classes, it is surprising to claim that there is no permanent rule and social position. To say that people's social status is reversible is to say that there is no high or low position that is held permanently.

This view directly reflects Ethiopia's understanding of society. While there are permanent classes, there is no position that individuals inherit by birth. Higher positions, especially, are taken up by individuals who come from lower positions. Ethiopians have called this ability to move from one class to another "luck." Luck reveals Ethiopia's social mobility.

Since transferring from lower to higher social positions is advancement, we may ask why, instead of calling it luck, Ethiopians did not call it talent. The answer is simple. Talent requires being chosen by God, since it is bestowed by Him. Since we can think of what we receive from God only as a gift or allotment, and not as something we deserve, the right view is the one that speaks of luck.

It is clear that the concept of fate is interlinked with the Ethiopian conception of time. The cyclicality of time opens doors for opportunities. There are varying higher and lower social positions. However, these positions are held by individuals not permanently, but in turn. Because the law of rotation demotes those who have been promoted, permanent positions do not exist. Thus, the opportunity for a person in a lower position to replace someone in a higher position is made available.

The impossibility of having permanent lines of gentry and kingship, as in Europe, is proven by Ethiopia's long history. If we start with the king, no Ethiopian king was able to keep power in his family line. This does not mean that no son of a king has ever inherited the throne. Rather, ascent to the throne was not so much a special right as an outcome of victory over competitors. His victory revealed his destiny, that is, the fact that he was chosen by God. Because of this, in Ethiopia, a son of a *kosso* seller, as Tewodros was, could become king.†

As many studies show, in Ethiopia, there was not a rigid separation between peasantry and gentry as there was in Europe. What created difference between individuals was their holding a position as a result of individual

እዚህ ላይ ነው በኃይለ ሥላሴ ዘመን ከባድ ከባሕል ውጪ የሆነ አሠራር መጀመሩን የምናየው። ንጉሡ የራሳቸውን ቤተሰብ ልዩ በማድረግ ሥልጣን በአልጋ ወራሽነት ለልጃቸው እንዲተላለፍ ደነገጉ። ድንጋጌው የጊዜን ተፈራራቂነት በመሻር ሥልጣንን ለተወሰነ ቤተሰብ በቋሚነት የሰጠ ነው። የሰሎሞን ዘር የሚለውን በኃይለ ሥላሴ ዘር በመተርጎም ለአገሪቱ ባዕድ የሆነ ሥልጣንን የማውረስ ልዩ መብት የፈጠረ ነው። በቅድመ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የኢትዮጵያ አንድነት ስሜት አንዱ ምንጭ ይኸው ለዋናው ዙፋን የተለያዩ ክፍሎች የነበራቸው እኩል መብት ነበር።

ከፈረቃዊ ወደ ግባዊ ጊዜ

የኢትዮጵያን የጊዜ ግንዛቤ በፈረቃዊ አመለካከት መወሰን ስህተት ይሆናል። የክርስቲያን ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ኢትዮጵያውያን እንደ ማንኛውም ክርስቲያናዊ ባህል ጊዜ ወደ አንድ ግብ እንደሚያመራ ያምናሉ። የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ኢትዮጵያውያንም የጊዜን ግባዊነት ይቀበላሉ። ፈረቃ ወደ ፊት የማይሄድ፤ አዲስ ለውጥና መሻሻል የማያሳይ ድግምግሞሽ ነው። ሂደት ግባዊ ሲሆን በአንድ አቅጣጫ ከመጓዙም በላይ የሚያከናውነው ዓላማ አለው።

እግዜር ዓለምን ሲፈጥር አብሮ ሂደቱን ቀይሷል። ዓለም መጀመሪያ እንዳለው ሁሉ መጨረሻም ይኖረዋል። መጨረሻውም በክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ይፈጸማል። በመሆኑም የጊዜና የታሪክ ሂደት የሚደጋገም ብቻ ሳይሆን ወደ ፍጻሜም የሚያመራ ነው። ፍጻሜውም ወደ የተሟላ ኑሮ ደርጃ የሚያሸጋግር እንጂ የመኖር ማለቂያ አይደለም።

እዚህ ላይ ነው የኢትዮጵያውያን አመለካከት ከሌሎች አፍሪካውያን በግልጽ የሚለየው። እንደ አፍሪካዊው ፈላስፋ ጆን ምቢቲ አባባል የአፍሪካውያን የጊዜ ግንዛቤ ከአውሮፕዊው የተለየ ነው። አውሮፓውያን ጊዜ ሶስት ማዕዘናት አሉት ይላሉ፡፡ እነሱም ያለፈው፤ አሁን ያለውና መጪው ናቸው። ለአፍሪካዊውን ግን "ጊዜ በረጅም ያለፈ፤ አሁንና መጪነት እስከ ማጣት የሚደርስ የሁለታዊ ማዕዘን ክስተት ነው።"[8] ክርስቲያናዊ አመለካከት ኢትዮጵያውያን፤ ልክ እንደ አውሮፓውያን፤ መጪውንና ወደ እጅግ የበለጠ ኑሮ የሚያሸጋግረውን ፍጻሜ የሚጠባበቅ የጊዜ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አድርጓል። የጊዜን ጠባይ በሶስት ማዕዘናት በማየታቸውም ለኢትዮጵያውያን ጊዜ ግባዊ ክስተት ሆኗል።

ልንክድ የማንችለው ፈረቃዊ ግንዛቤ ከግባዊ ግንዛቤ ጋር እንደማይጣጣም ነው። የጊዜ ሂደት እንዴት በአንደነት ፈረቃዊም ግባዊም ሊሆን ይችላል? ፈረቃ በራሱ የሚገለባበጥ ግበቢስ ሂደት ከመሆኑ ሌላ የእግዜርን ዘወትር ጣልቃገቢነት አይጠይቅም። ለእንዲህ ያለ ተመላላሽና አቅጣጫ የሌለው ሂደት ግብ ማስቀመጥ በእርግጥም ተቃራኒ አነጋገር ይመስላል። ለዚህም ነው ይህን ዓለም ከንቱ በማድርግ ከበደ ሚካኤል "የዚህ ዓለም ነገር ምንም የለው መላ" ያለው፡፡[9]

በፈረቃዊና በግባዊ ሂደት መካከል የሚታየው አለመጣጣም ለኢትዮጵያውያን ግን እውን አይደልም። በጥሞና ብናስበው፤ ተፈራራቂ ሂደት ላይ ግብ ሲታከል የሚሰጠን የፈረቃው በድንገት መቋረጥን ነው። ይህም ማለት እግዜር የጀመረውን ሂደት በገዛ ፈቃዱ በድንገት ያቆማል ማለት ነው። አውሮፓውያን እንደሚሉት ጊዜ የሚቆመው የተሻለ ሁኔታ ስለተፈጠረ አይደለም። እግዜር በቃ ስለሚል ብቻ ነው። የፈረቃው ሁሌም መቀጠል የሚያመለክተው



fate, rather than because of bloodline. The farmer or peasant, because of his fate, became a payer of duties, but that did not make him a lower person. He therefore unceasingly wished that someday his fate would change and that he would gain someone's higher position.

It is here that we see the beginning of a radical shift from tradition during Haile Selassie's reign. Assigning a special status to his family, the king proclaimed that power would go to his son as the sole heir to the throne. This declaration abolished the cyclicality of time and gave power to a particular family permanently. By equating Solomon's genealogy with Selassie's, it created a special right of transmission of power that was alien to the country. One of the sources of the pre–Haile Selassie sentiment of Ethiopian unity was the equal right of different regions to accede to the throne.

FROM CYCLICAL TIME TO TELEOLOGICAL TIME

To reduce Ethiopia's understanding of time to cyclicality would be a mistake. Like any Christian people, Ethiopians believe that time moves toward a single goal. Followers of Islam in Ethiopia accept the goal-oriented nature of time as well. Cyclicality is a repetition that does not move forward or show change and improvement. A goal-oriented process not only moves in one direction but also has a purpose to accomplish.

When God created the world, He also planned its process. Just as the world has a beginning, it also has an end. The end will arrive with the second coming of Christ. Thus, not only is the process of time and history not repetitive, but it also heads toward an end. The end is not the end of life but rather its transition to a higher form.

This is where the Ethiopian outlook is different from other African outlooks. According to John Mbiti, the African's conception of time is different from that of the European. Europeans say time has three dimensions. These are: past, present, and future. But for Africans, "time is a two-dimensional phenomenon, with a long *past*, a *present* and virtually no *future*."[8] Just as in the case of Europeans, Christianity has enabled Ethiopians to have a conception of time that anticipates the coming and the transition to a greatly superior life. Since they saw the three-dimensional nature of time, time for Ethiopians became a teleological occurrence.

It is undeniable that the cyclical conception does not agree with the teleological conception. How could the trajectory of time be cyclical and teleological at the same time? In addition to being a goalless process that turns on its own, cyclicality does not require the intervention of God. Indeed, to give a goal to an oscillating and directionless process appears to be contradictory. This is why Kebede Mikael expressed the vanity of the world by saying: "The nature of this world is unpredictable."[9]

The opposition between cyclical and teleological process is, however, not real for Ethiopians. If we think deeply about it, what results from the insertion of a goal into a cyclical process is its sudden interruption. This

ሰዎች በራሳቸው ፍላጎትና ጥረት የሚደርሱበት የተሻሻለ ሁኔታ መቼም እንደማይኖር ነው። የሚሠሩትን ሁሉ መልሰው ስለሚያበላሹ፤ በገዛ ጥረታቸው ከፈረቃ ሕግ መቼም አይላቀቁም።

በመሆኑም የጊዜ መጨረሻ የእግዜርን ፍጹም ሥልጣን ገላጭ ነው። በራሱ ፈቃድ የትም የማይደርሰውን ድግምግሞሽ እግዜር ሲያቆም ብቻ ነው ሰዎች ከፈረቃ የጸዳ ቋሚ ወይም ዘለዓለማዊ ኑሮ የሚኖራቸው። ሕይወት የማይለዋወጥ፤ ውጣ ውረድ የሌለው የሚሆነው፤ ሰዎች የእግዜርን ዘለዓለማዊ ፍቅር ሲያገኙ ብቻ ነው። ስለሆነም የጊዜ መጨረሻ ከፈረቃዊ ኑሮ መላቀቅ ወይም መዳን ማለት ነው።

የከብረ ነገሥትን ልዩና ትልቅ መልዕክት የምናገኘው እዚህ ላይ ነው። እሱም ነገሮች ሁሉ በድግምግሞሽ ሕግ ሲገዙ ኢትዮጵያ ብቻ የተለየ ዕጣ ወይም ዕድል አላት የሚል ነው። እነጋገሩ ኢትዮጵያን ከውጣ ውረድ ደንብ በማግለል በመጨርሻ ጠላቶቿን በሙሉ አሸንፋ ብቻዋን ትቀራለች ይላል። በሌላ አባባል፤ ነገሥታት ሁሉ በተራ ሲነሱና ሲወድቁ ኢትዮጵያ ከፈረቃዊ ጊዜ በመላቀቅ በድል ጸንታ "እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ትኖራለች።"[10]

ከብረ ነገሥት ይህን እምነት የሚያፈልቀው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሰፈረው የዳዊት መዝሙር በመነሳት ነው። "ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች"[11] የሚለው የዳዊት ትንቢት እንደ ከብረ ነገሥት አባባል የሚያመለከተው ኢትዮጵያ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ጸንታ በድል አድራጊነት እስከ ጊዜ ፍጻሜ፤ ማለትም እስከ ክርስቶስ መምጫ ደረስ እንደምትቆይ ነው። ምንም ሊያጠፉት እንደማይችል ሲገልጽም፤ ሃሳዊ መሲህ በሚመጣበት ጊዜ እንኳን አትጠፋም ወይ ተብሎ ሲጠየቅ፤ የከብረ ነገሥት መልስ በፍጹም አትጠፋም ነው። ምክንያቱም "ዳዊት 'ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሄር ትዘረጋለች' ሲል ትንቢት አልተናገረም" ወይ?[12]

እርግጥ ነው፤ ኢትዮጵያም የምትወደቅባቸው ጊዜያቶች ይኖራሉ። ነገር ግን መቼም ቢሆን ወድቃ አትቀርም። የምትውድቀውም በገዛ ጥፋትዋ ስለሆነ ውድቀቷ የእግዜር ቅጣት ይሆናል። ለምሳሌ የጣሊያንን ወረራ እንደ አምላካዊ ቁጣ በመተርጎም ከበደ ሚካኤል እንዲህ ብሏል።

> እግዜር አዞት ሕዝቡን አምስት ዓመት ቀጣ፤
> ትእዛዙን ፈጽሞ በቃህ ሲለው ወጣ።[13]

እግዜር እራሱ የወሰነውን የውድመት መጨረሻ ለምን ኢትዮጵያ ላይ ያፈርሳል? ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሰጥ አሁንም ከብረ ነገሥት ነው። እስራኤላውያን ክርስትናን ባለመቀበላቸው ኢትዮጵያ እስራኤልን በመተካት የአምላክ ምርጥ አገር ሆናለች። ሹመቱም ኢትዮጵያን ከፈረቃ ሕግ በመከለል ልዩ ዕድል ይሰጣታል። ምርጥ ለሆነች አገር እግዜር ልዩ እንክብካቤ ያደርጋል ማለት ተገቢ ነው። እግዜር ኢትዮጵያን የታቦት ባለቤት በማድረግ ልዩ ሥፍራ እንደሰጣት ከብረ ነገሥት ሲያረጋግጥ እንዲህ ይላል፤ "እግዚአብሄር ለኢትዮጵያ ንጉስ እንደዚህ ያለ ከብርና ግርማን አደርገ። ስለ እግዚአብሄር ታቦተ ህግ ስለ ሰማያዊቷ ጽዮንም ከምድር ነገስታት ሁሉ ከፍ ከፍ አደረገው። እግዚአብሄር መንፈሳዊት ፈቃዱን እንድንፈጽም ያብቃን።"[14] አነጋገሩ የኢትዮጵያ ልዩ ሥፍራ የመነጨው ከአምለክ ፈቃድ መሆኑን በግልጽ ያስቀምጣል።



means that God will suddenly stop, by His own will, the cyclical process that He started. Time does not stop because a better situation is created, as the Europeans say. It will stop because God says, "Enough." The continuation of cyclicality shows that humans will never reach a better situation by their own effort. Since humans destroy what they have built, they can never escape, by their own efforts, from the law of cyclicality.

Thus, the end of time reveals God's absolute power. Only when God stops the directionless repetition of time will humans have a fixed or eternal life that is free of cyclicality. Life becomes unchanging and free from ups and downs only when humans receive God's eternal love. Thus, the end of time signifies freedom from cyclical life, that is, it signifies salvation.

We find here the special and important message of the *Kebra Negast*. This message is that, while all things are ruled by the law of repetition, only Ethiopia has a special fate. This message removes Ethiopia from the norm of ups and downs by stating that she will vanquish all her enemies and remain the last one standing. To put it another way, while kings rise and fall by turn, Ethiopia, because she has been delivered from cyclical time, will remain victorious and "will live until the end of time."[10]

The *Kebra Negast* derives this belief from the part of the Bible dealing with the Psalms of David. According to the *Kebra Negast,* David's prophecy, "Ethiopia shall stretch her hands unto God," indicates that Ethiopia, staying faithful to the Orthodox religion, will remain victorious to the end, that is, until the coming of Christ.[11] Nothing can destroy Ethiopia; even when asked whether Ethiopia will not disappear when the false prophet comes, *Kebra Negast*'s answer is "absolutely not." For, "has not David prophesied that Ethiopia shall stretch forth her hands unto God?"[12]

True, there will be times when Ethiopia falls down. However, Ethiopia shall never remain fallen. When she falls, it is her own fault; as such, her fall is God's punishment. For example, interpreting the Italian invasion as God's anger, Kebede Mikael said:

> God ordered the punishment of the people for five years
> Accomplishing His order, it [Italy] left when God said enough[13]

Why would God break with His plan of total destruction by excluding Ethiopia? Once again, the *Kebra Negast* provides the answer. Since the Israelites did not accept Christianity, Ethiopia replaced Israel and became God's chosen country. This election protects Ethiopia from the laws of cyclical time by giving her a special destiny. It is appropriate to maintain that God provides special care for His chosen country. Confirming that God gave Ethiopia a special place by making her the keeper of the Ark, the *Kebra Negast* says: "God confers such honor and grace on the Ethiopian king. Due to God's Ark and the heavenly Zion, He raised him higher than all the kings of the world. May God help us fulfill His spiritual will."[14] This statement clearly shows that Ethiopia's special place came from God's will.

የክብረ ነገሥት አባባል የሚያሳየው ኢትዮጵያ የራሷ የሆነ የታሪክ ንድፈ-ሐሳብ እንደነበራት ነው። ታሪኩም የተቀመረው ኢትዮጵያን እምብርት አገር በማድረግ ሁሉም ነገር፤ የሌሎች አገሮች ታሪክ ጭምር፤ ወደ እሷ ድል አድራጊነት እንደሚያመራ በማስቀመጥ ነው። የዓለም ታሪክ በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት መደምደም የልዩ ዕድል ባለቤት መሆኗን ያረጋግጣል። አሁን እንደሆነው የሌሎች አገሮች ታሪክ ተከታይ መሆኗ ቀርቶ ሌሎች አገሮች በእሷ ታሪክ ይመሩ ነበር ማለት ነው። የክብረ ነገሥት ትልቁ መልዕክት ኢትዮጵያን የታሪክ መሪ ኃይል ማድረጉ ነበር።

## ኢትዮጵያና ዘመናዊነት

የኢትዮጵያ የታሪክ ባለቤትነት ዘመናዊ ሥልጣኔ ከገባ ጀምሮ ማብቃቱ አይካድም። የታሪክ መሪነቷን በምዕራባዊ አገሮች ከተቀማች ጀምሮ፤ በተለይ ምዕራባዊ ትምህርት በቀመሱ ኢትዮጵውያን ዘንድ ኢትዮጵያ የምትታየው እንደ ኋላቀር አገር ነው። እንዲህም በመታየቷ የምዕራባዊ አገሮች ተከታይና ቀጂ ሆናለች። ተከታይነቷ በምጣኔ ሀብትና በቴክኖሎጂ መስክ ብቻ ሳይሆን በባህልም ጭምር ነው።

ይህ እንዴት ሆነ ቢባል መልሱን የሚሰጠን የአውሮፓውያን ትምህርት ካለምንም ገደብ የመለቀቅ ሁኔታ ነው። ትምህርቱ የተመሰረተበት የታሪክ ንድፈ-ሓሳብ የአውሮፓውያን አመለካከት፣ ፋይዳና ማህበራዊ ሥርዓት ተቀዳሚ በማድረግ አውሮፓዊ ያልሆኑ ባህሎችና አሠራሮችን ሁሉ ኋላቀር ያደርጋል። ከዚህም አልፎ ሌሎች አገሮች ሊሠለጥኑ የሚችሉት አውሮፓን በአርአያነት ሲከተሉ ብቻ ነው ይላል፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵውያን ዘመናዊ የሚሆኑት ከራሳቸው ታሪክና ባህል ወጥተው በምዕራባዊነት ሲጠመቁ ብቻ ነው።

ው ታላቁ ፈላስፋ ሄገል እንዳለው: "የዓለም ታሪክ የሚጓዘው ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ነው፤ ምክንያቱም አውሮፓ የመጨረሻ የታሪክ ግብ ነች።"[15] ይህንን የታሪክ አቅጣጫ ኢትዮጵውያን ስለተቀበሉት መጪውን ማሰብ የቻሉት ኢትዮጵያዊነትን በማሻሻልና በማሳደግ ሳይሆን ወደ ምዕራባዊነት በመቀየር ነው። የአውሮፓ ትምህርት ዋና ውጤት ለራስ ታሪክና ባህል ባይተዋር መሆን ነው።

በዘመናዊ ትምህርት ከባድ ተጽዕኖ የተነሳ ኢትዮጵውያን ለእነሱ የሚበጀውን የጊዜ ተፈራራቂ ጠባይን ወደ ጎን አደረጉት። ጥቅሙ የት ነው ብለን ብንጠይቅ መልሱ አያስቸግርም። ፈረቃዊ ጊዜ የሚለው ሁሉም ጊዜው ይመጣል፤ ማንም አገር ታሪክን በቋሚነት አይመራም ነው። የተነሳ ሁሉ ይወድቃል፤ የወደቀም ይነሳል። ገናናነት ሁሌም ጊዜያዊ ነው። በመሆኑም፤ የታሪክ መሪነትን በፈረቃ እንጂ ማንም በቋሚነት አይዘውም።

ለዚህም ይመስላል ኢትዮጵያውያን የምዕራባዊ ሥልጣኔን መጀመሪያ ሲሰይሙት "ዘመናዊ ሥልጣኔ" ያሉት። ዘመናዊ ሲሉ ጊዜ ያመጣውና ኃላፊ ማለታቸው ነበር፡፡ ይህን ሲሉ ደግሞ ኋለቅር አይደለንም፤ ጊዜ ባመጣሽ ሥልጣኔ ለጊዜው ተገፋን እንጂ ማለታቸው ነበር። የአውሮፓ አሁን ገናናነት በውድቀት ይተካልና አውሮፓን ማየት መከተል እንዳለብን ደንብ ሳይሆን እንደ ተቀናቃኝ ነው። በእርግጥ ከተቀናቃኝ ብዙ መማር አለብን፤ ትምህርቱን የምንወስደው ግን እሱን ለመምሰል ሳይሆን እራሳችንን ለአዲስ ለውጥና ሁኔታ አላምደን እሱን ለመብለጥ ነው።



What the *Kebra Negast*'s statement shows is that Ethiopia had her own theory of history. By making Ethiopia the center of the world, the historical scheme was designed in such a way that all things, including other countries' histories, march toward the realization of her victory. That world history was to conclude with Ethiopia's victory proves that she had a special destiny. This means that, unlike the present situation making Ethiopia the follower of other countries' histories, other countries used to be led by her history. The greatest message of the *Kebra Negast* is that it makes Ethiopia history's leading force.

## ETHIOPIA AND MODERNITY

It cannot be denied that Ethiopia's ownership of history has ended since the coming of modernity. Ever since her leadership in history was snatched away by Western countries, Ethiopia has been seen as a backward country, especially by Ethiopians who have tasted Western education. Because of this perception, she has become the follower and copier of Western countries. She has become a follower not only in the fields of economics and technology but also in that of culture.

If it is asked how this happened, the answer lies in the situation that allowed European education to spread unhindered. The theory of history upon which this education was based privileges the European viewpoint, values, and social order, thereby defining non-European cultures and ways of doing things as backward. In addition, it declares that other countries can becomes civilized only when they follow Europeans as their example. Accordingly, Ethiopians become modern only when, abandoning their history and culture, they convert to Westernism.

As the great German philosopher Hegel said: "The History of the World travels from East to West, for Europe is absolutely the end of History."[15] Since Ethiopians have accepted this trajectory of history, they have come to think about the future not in terms of improving and cultivating Ethiopianism, but in terms of converting to Westernism. The main result of European education is to be alienated from one's history and culture.

Because of the heavy influence of modern education, Ethiopians have put aside the cyclical nature of time, which had been beneficial to them. If we ask what its benefit is, the answer is not difficult. What cyclical time tells us is that everybody's time will come; no country will permanently lead history. All those who were up will fall and those who were down will rise. Greatness is always temporary. Thus, leadership of history is held by turn; no one holds it permanently.

It seems that is why Ethiopians, when they first named Western civilization, called it "modern civilization." By "modern," they meant something that time brings, that is, and something that is transient. In so saying, they implied that they were not backward; rather, they were temporarily pushed back by a civilization that time brought. Since Europe's current prominence will be replaced by downfall, we should see Europe not as a model to follow but as an opponent. To be sure, we should learn a lot from an opponent;

## ዘመናዊነትና ተሐድሶ

የታሪክን መመላለስ ኢትዮጵያውያን አቅይተው ቢሆን ኖሮ እራሳቸውን ኋላቀርና የሌሎ አገሮች ታሪክ ተከታይ አድርገው ከማሰብ ባመለጡ ነበር ብለናል። የምዕራባዊ ታሪክ አቀራረጽ የሚያስተምረው አውሮፓን መከተልና መቅዳት በመሆኑ ራስን መቻልንና የፈጠራ ችሎታን ማዳበር አያበረታታም። ተደጋጋሚ የጊዜ ግንዛቤ ግን በአንድ መሥመር የሚሄድ ባለመሆኑ መጎተትን ሳይሆን ተራ መጠበቅን ነው የሚያስተምርው። ለተነሳ ሁሉ መውደቅ አይቀሬ ነው ስለሚል ለሁሉ የመነሳት ዕድል ይሰጣል።

ይህም በታሪክ የተመሰከረ እውነታ ነው። አውሮፓ ኋላቀር በነበረበት ጊዜ የኤዢያና የአፍሪካ ሕዝቦች ከፍተኛ ሥልጣኔዎችን አሳይተዋል። ዘመናዊ ታሪክን ብንወስድ የአውሮፓ ፍጹም ኃይል በአሜሪካን ገናናነት ተዳክሟል። የዘመናዊ ጃፓንና ቻይና አካሄድ መልሶ የኤዢያን የበላይነትን የሚያመቻች ይመስላል።

አንድ አገር ተራ የሚያገኘው ደግሞ ሌላውን ተከትሎ ምንነቱን ሲያጣ አይደለም። የራሱን ባሕርያት በማደስ መሻሻል ሲያሳይ ብቻ ነው፤ ምክንያቱም የሌላ ቅጂ ሆኖ እስከቀረበ ድረስ የሚጫወተው አዲስና የላቀ ሚና አይኖረውም። ዋናው የያዘውን ሥፍራ የበታች የሆነው ቅጂው ሊነጥቅ አይችልም። ተጎታች ልዩነትን ካላመነጨ መቼም ቢሆን ጎታች አይሆንም።

እራስን ማሻሻል ሌላን መቅዳት ሳይሆን እራስን ማደስ ነው። ይህም የሚሆነው ወደ ኋላ፤ ወደ ራስ ሥልጣኔ ምንጭ በመመልስ ነው። ሂደቱ ዳግም ትውልድ የሚባለውን የለውጥ አቅጣጫ ያመጣል። ወደ ኋላ የሚኬደው የድሮውን፤ ያለፈውን ለመመልስ አይደልም። ወደ ራስ ታሪክ ምንጭ መመለስ መንፈሳዊ ቅስቀሳ ከመስጠቱም በላይ የተጣራ አመለካከት ያስገኛል።

በግልጽ እንደሚታየው ዘመናዊነትን እንደ ዕድሳት ለማየት በመጀመሪያ ደረጃ ከአውሮፓ በአንድ መሥመርና አቅጣጫ ከሚሄደው የታሪክ ግንዛቤ መላቀቅ ይጠይቃል። መተካት ያለበትም የጊዜን መደጋገም በሚያስተምረው አመለካከት ነው። በአንድ አቅጣጫ መሄድ ቀርቶ ጊዜ የሚደጋገም ከሆነ የመታደስን ሁኔታ ይፈጥራል። የጠፋ መንገደኛ ወደ መነሻው ለመመልስ ይጥራል እንጂ በያዘው ስህተት ዝም ብሎ አይቀጥልም። አቅጣጫ የጠፋው ግለሰብ ወይም ሕብረተሰብም መፍትሄ የሚያገኘው ወደ ታሪኩ መነሻ ሲመለስና መሠረቱን መልሶ ሲጨብጥ ነው። እንዲህ በመመለሱ ደግሞ ከመንከራተት መላቀቁ ብቻ ሳይሆን እንደገና ይታደሳል፤ ይወለዳል።

ይህ የሚያሳየው የድግምግሞሽ ምስጢር መታደስ መሆኑን ነው። ሕይወት እራሱን የሚያድሰው ወደ ኋላ በመመለስ አይደለም ወይ? ያደገው የሚታደሰው እንደገና ሕጻን በመሆን ነው። ተፈጥሯዊ ነገሮች ሁሉ የሚታደሱት በአንድ የማይቀለበስ አቅጣጫ ከመሄድ ይልቅ የመደጋገም ጠባይ ስላላቸው ነው። የተበላሸው እንደገና ይጠራል። የደከመው እንደገና ጉልበት ያገኛል። የታጨደው መልሶ ይበቅላል። የታወቀው ሲሻር እውቀት ይታደሳል።

ሥልጣኔዎች የሚወድቁት በየጊዜው በሚያከማቿቸው ስህተቶችና መጥፎና ጎታች ልምዶች በመሆኑ ከራስ ታሪክ መሥመር ሳይወጣ የሥልጣኔ ጽዳት ማድረግ የሚቻለው ወደ ምንጩ በመመለስ ነው። የመመለሱ ሂደት ትክክለኛውን መሠርት እንደገና ያስቀምጣል፤ እስካሁን



however, we learn not to look like our opponent but to adapt ourselves to a novel situation of change so as to supersede him.

## MODERNITY AND RENEWAL

We said before that if Ethiopians had kept the thought of the repetition of history, they would have escaped from thinking of themselves as backward and as followers of other countries' histories. Since Western history is designed to teach people to follow and copy Europe, it does not encourage independence and the cultivation of creativity. The concept of cyclical time, since it does not travel in a single direction, teaches one not to be pulled but to wait one's turn. Since it says that whatever is up must fall down, it gives everybody a chance to rise.

This is a truth that is proven by history. When Europe was backward, the peoples of Asia and Africa displayed high civilizations. If we take modern history, Europe's absolute power has been weakened by America's might. The trend of modern Japan and China seems to prepare the restoration of Asia's dominance.

A country does not get its turn if it loses its identity by following another country. It does so only when it shows improvement by renewing its characteristics. Evidently, as long as it presents itself as a copy of another, it will not have a new and better role to play. The place occupied by the model cannot be appropriated by its copy. Unless the one being pulled brings difference, it can never become the one who pulls.

Self-improvement is not copying another: it is renewing oneself. This happens by going back, that is, by going to the source of one's own civilization. This movement will bring a change of direction, which is known as "renaissance." To go back is not to bring back the old and the past. To return to one's source of history not only provides spiritual awakening but also begets a clear perspective.

Clearly, in order to see modernity as renewal, it is necessary, as a first step, to break with Europe's understanding of history, which travels in a single line and direction. What we need in its place is the perspective that teaches the repetition of time. If, instead of going in one direction, time is cyclical, a situation conducive to renewal is created. A lost traveler attempts to return to his point of departure; he does not continue on the same mistaken path. A lost individual or society finds its path when it returns to its historical beginnings and grasps its foundation. To return in this manner not only saves from it wandering but also produces renewal and rebirth.

This reveals that the secret of repetition is renewal. Does not life renew itself by going back? The adult is renewed by becoming a child again. All natural things are renewed because, rather than going in one irreversible direction, they have a repetitive character. In this way, that which is damaged is recreated. The weak regain strength. That which is reaped will grow again. When the known becomes obsolete, knowledge is renewed.

Since civilizations fall because of the mistakes and depraved habits that they accumulate over time, the way to purify one's civilization without abandoning its proper historical trajectory is by returning to its source. This

የተያዘውን የተሳሳተ አቅጣጫ ያርማል። ወደ ኃላ መመልስ ማጽዳትንና ለዳግም ትልቅነት መዘጋጀት ያስከትላል። በዚህ አባባል ዘመናዊነት ዳግመትውልድ ይሆን ማለት ነው።

ለዚህ አመለካከት ጥሩ ምሳሌ ጃፓን ናት። የዘመናዊነትን ጉዞ ጃፓን የጀመረችው አውሮፓን በመከተል ሳይሆን ወደ እራሷ ታሪክ ምንጭ በመመለስ ነው። ይህ ሂደት ነው የሜኢጂን ሥልጣን የመለስና የንጉሡን መለኮታዊ መልክ ያደሰ። መመለሱ የዘመናዊነት ጥረትን በንጉሡ የተደገፈ ስላደረገ የሚያስፈልጉት ማህበራዊና የምርት ዘዴ ለውጦች በንጉሡ ፈቃድ ስም በቀላሉ ሊከናወኑ ችለዋል። የዘመናዊነት ሂደት ባሕላዊ የሆነውን በንጉሡ መለኮታዊ መለያ በመባረኩ ሂደቱ ሰፊ ተቀባይነት ከማግኘቱ ሌላ ከፍተኛ የማስፈጸምና የመፈጸም ጉጉት በጃፓኖች ዘንድ ፈጥሯል።

አውሮፓውያንም የዘመናዊነት ሂደትን መጀመራቸውን ያበሰሩት ወደ ሥልጣኔያቸው ምንጭ በመመለስ ነው። ረጅምና ጨለማ ከነበረው የፊውዳል ሥርዓት ለመላቀቅ የቻሉት ወደ ጥንት ግሪክና ላቲን ሥልጣኔውች በመመልከት ነው። ይህንንም የለውጥ አቅጣጫ "ዳግማዊ ውልደት" ብለውታል። እንዲሁም በሃይማኖት በኩል የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ የጀመረው እውን ወደ ሆነው ክርስቲያን እምነት እንመልስ በማለት ነው። ያለው እምነት የተሳሳተና በመጥፎ ልምዶች የተበከለ በመሆኑ ወደ ምንጩ በመሄድ መታደስ አለበት የሚለውን ሂደት ነው አውሮፓውያን በቀጥታ "ተሐድሶ" ያሉት።

ኢትዮጵያ ውስጥ የተቀየሰው ሂደት ግን እንደገና መወለድ ሳይሆን ከራስ ምንነትና ታሪክ በመውጣት ሌሎች አገሮችን ተከተል የሚል ነው። በኃይል ሥላሴ ዘመን ኢትዮጵያ የአውሮፓን ትምህርት ካለ ገድብ በመቀበል ምዕራብ አገሮችን ተከተለች። የዚህ ትምህርት ውጤት የሆነው ዘመናዊ ትምህርት የቀመሰው ትውልድና የደርግ መንግሥት ደግሞ የምሥራቁ፤ ማለትም የሶሺያሊስት ዓላማ ብቻ ይበጃል በማለት፤ ወደባስ ስህተት አገሪቱን ጨመሯት። የምዕራባዊ ታሪክ ንድፈሓስብን ከመውረስ ይልቅ ኢትዮጵያዊ የሆነውን የጊዜ ተፈራራቂነት ተከትለን ቢሆን ኖሮ የዘመናዊነትን ችግሮች ወደ ኋላ፤ ወደ ምንጫችን በመመልስ ልንፈታቸው በሞከርን ነበር። ዘመናዊነት ዕድሳት እንጂ ከራስ መውጣት ባልሆነ ነበር።

ከሁሉም በላይ ድግምግሞሻዊ የጊዜ አመለካከት የፉክክርን ስሜት ያዳብራል። እንደ ምዕራባዊው ግንዛቤ ጊዜ በአንድ መሥመር ብቻ ስለማይሄድ አንድን መሪ ሌላውን ተከታይ አያደርግም። ይልቁንም ሁሉ ነገር ይደጋገማል ስለሚል ከመነሻው መፎካከርን ያመቻቻል። አሁን መሪ የሆነው ወዳቂ ነው ስለሚል ተራ ጠብቆ የመተካትን ስሜት ያመነጫል። የሚለው ተከተል ሳይሆን ለመተካት ተዘጋጅ፤ ዕድልህን አመቻች ነው። ምዕራባውያን እኛን ብትከተሉ ለሁሉ የሚበጅና የሚበቃ ዓላማና ብልጽግና አለን እያሉ ሲሰብኩ ፈረቃዊ አመለካከት ግን ሁሉንም የሚያስደስት ሁኔታ ስለሌለ የታሪክን ሂደት ማየት ያለብን እንደ "ሻሞ" ጨዋታ ነው ይላል።

የኃይል ሥላሴን ሥርዓት የገለበጠው እንቅስቃሴ እራሱን የተመለከተው እንደ ተሐድሶ ሳይሆን እንደ አብዮት ነው። የተፈለገውም ሥርነቀል ለውጥ እንጂ ዕድሳት አልነበረም። ለምን ሥርነቀል ለውጥ ተፈለገ ብለን ብንጠይቅ መልሱን የሚሰጠን የነበረው ዓላማ ኢትዮጵያዊነት ማልማት ሳይሆን አርአያ ናቸው በተባሉ አገሮች አንጻር አትዮጵያን መቅረጽ መሆኑን ስናጤን ነው። ተሐድሶ ለማሰብ በአራስ ምንነትና ታሪክ ውስጥ መቆየት ይጠይቃል። ስርነቀል ለውጥ ለመመኘት ግን ለአራስ ባዕድ መሆንና የሌል አገር ተንታች ሆኖ መቅረብ ያሻል። ይህን አመለካከት የሚቀርጸው ከዘመናዊ ትምህርት የሚወሰደው የአውሮፓ የጊዜና የታሪክ



return reinstitutes the correct foundation; it corrects the mistaken direction that has previously been pursued. Return results in purification and preparation for renewed greatness. This suggests that modernity just is renaissance.

A good example of this is Japan. Japan started her path to modernity not by following Europe, but by returning to the source of her own history. It was this movement that allowed for the Meiji Restoration and the renewal of the emperor's position as a divine figure. Since the return signified that the attempt to modernize had the emperor's sanction, it facilitated the implementation of necessary social and economic changes in the name of the emperor. Because modernization was approved by the traditional belief in the divine nature of the emperor, it not only gained wide acceptance but also created great eagerness among the Japanese for its realization.

Europeans also announced the beginning of their modernization by returning to the source of their civilization. They were able to break with the long and dark era of feudalism by turning to ancient Greek and Roman civilization. They called this change of direction "renaissance." Likewise, on the religious front, the Protestant movement started on the ground that it had become necessary to return to the true faith. Since the existing faith had become tainted with bad and incorrect habits, Europeans called the movement to go back to the source so as to renew it the "Reformation."

But the movement that was initiated in Ethiopia advocated, not rebirth, but the desertion of selfhood and history by following other countries. During Haile Selassie's time, by accepting European education without any limits, Ethiopia followed Western countries. The results of this education, that is, the generation that tasted modern education and the Derg regime, claimed that only the Eastern, or socialist, goal was good, thereby putting the country in a worse situation. If, instead of inheriting the Western theory of history, we had followed the Ethiopian conception of cyclical time, we would have attempted to solve the problems of modernity by going back to our source. Modernity would have been renewal rather than denial of self.

More than anything else, the repetitive concept of time encourages the feeling of competition. Unlike the Western conception, it does not move in a single line, and so does not allow for one to be a leader and the other to be a follower. Rather, since it says that everything repeats, repetitive time encourages competition from the beginning. Since it says that the one who is a leader now will fall, it invites one to wait one's turn. It does not say, become a follower, but be ready to fill in, prepare your destiny. While the Europeans preach that, if you follow us, we offer comprehensive goals and prosperity for all, the cyclical view says that since there is no situation that can make everybody happy, we must see the movement of history as an up-for-grabs game.

The movement that overthrew Haile Selassie's rule saw itself not as renewal but as revolution. What they wanted was uprooting change rather than renewal. If we ask why uprooting change was sought, the answer is found in realizing that the goal was not to develop Ethiopia but to shape Ethiopia in accord with model countries. Obviously, what shaped this view is the European view of time and history taken from modern education

አንድ አገር ሊበለጽግ የሚችለው የራሱ ታሪክ ባለቤት ሲሆን ነው። የራሱ ታሪክ ባለቤት አንድ አገር ለመሆን የሚችለው ደግሞ በጊዜ ውስጥ እራሱን በማየት ለመኖሩ ሉዓላዊ የሆነ ትርጓሜ ሲሰጥ ነው። የዚህ ጽሁፍ አጀማመር እንዳመለከተው፤ ጊዜ የኑባሬ ተርጓሚ ከሆነ በሌላ አገሮች ታሪክ የሚኖር ሕዝብ ለእራሱ ፍችና ዓላማ የሌለው ሕዝብ ነው። ዓላማ ከሌለው ደግሞ ዘመናዊነትን ሊያራምድ አይችልም። የሚችለው የሌላ አገር ዘመናዊነት ጥገኛ ወይም ተለጣፊ መሆን ነው። የራስን የጊዜ ግንዛቤ ማጣት የራስን ዓላማ መነጠቅ ማለት ነው። የራሱን አቅጣጫ የጠፋው ሕዝብ ዘመናዊነትን ቢያጨመላልቅ ሊገርመን አይገባም።

NOTES

1. ማርቲን ሃይደገር፤ ቤዚክ ራይቲንግ (ሳንፍራሲስኮ፤ ሃርፐር ኤንድ ሮው፤ ፐብሊሸር፤ 1977) ገጽ 61። ትርጉም ከጸሐፊው።

2. ሃንሪ በርግሶን፤ ዕቮሪ (ፓሪስ፤ፐረስ ዩኒቨሲቴር ደ ፍራንስ፤ 1970) ገጽ 534። ትርጉም ከጸሐፊ።

3. ፓርመኒዲዝ፤ ዘፕሪሶክራቲክስ (ኒውዮርክ፤ ኦደሲ ፕሬስ፤ 1966) ገጽ 97። ትርጉም ከጸሐፊ።

4. በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የሚለው አጠራር የሚመለከተው ቀድሞ ሐበሻ ተብሎ የሚታወቀውን በአመዛኙ አርቶዶክስ ክርስቲያን የሆነውን የኢትዮጵያን ሰሜን ክፍል ነው። ሆኖም ምንም እንኳን የደቡብ ክፍል አመለካከቱን ባያመነጭም በሰሜኑ ባሕል መዘመትና መሰራጨት የተነሳ አመለካከቱ ጥቅል ኢትዮጵያን የሚወክል ሆኗል።

5. ከብረ ነገስት፤ ተርጓሚ ስርግው ገላው (አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፤ 1994) ገጽ 59።

6. እዛው ገጽ 60-61።

7. ከበደ ሚካኤል፤ የቅኔ አዝማራ (አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ፡ 1946) ገጽ 97-99።

8. ጆን ምቢቲ፤ አፍሪቃን ሪሊጂን ኤንድ ፊሎዞፊ (ኒውዮርክ፤ ፍሬዴሪክ ፐራገር፤ 1975) ገጽ 17። ትርጉም ከጸሐፊ።

9. ከበደ፤ የቅኔ አዝማራ፤ ገጽ 99።

10. ከብረ ነገስት፤ ገጽ 146.

11. መጽሐፍ ቅዱስ፤ "መዝሙረ ዳዊት" (አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፤ 1980) ገጽ 460.

12. ከብረ ነገስት፤ ገጽ 146

13. ከበደ፤ የቅኔ አዝማራ፤ ገጽ 35።

14. ከብረ ነገስት፤ ገጽ 149።

15. ጂ.ዊ. ኤፍሄ. ሄግል፤ ዘ ፊሎዞፊ ኦፍ ሂስትሪ (ኒውዮርክ፤ ዶቨር ፐብሊኬሽን፤ 1956) ገጽ 103። ትርጉም ከጸሐፊ።



A country prospers when it becomes the owner of its own history. A country becomes the owner of its history when it sees itself through time and gives an autonomous meaning to its existence. As pointed out at the beginning of this essay, if time is the interpreter of being, a people who lives by other countries' histories is a people without its own meaning and goal. Having no goal of its own, such a people cannot promote modernity. The only thing possible is for it is to become a dependent or a vassal of other countries' modernity. Losing one's own conception of time is to be robbed of one's own goal. We should not be surprised if a people who has lost its direction mucks up modernity.

NOTES

1. Martin Heidegger, *Basic Writings,* ed. David Farrell Krell (San Francisco: HarperCollins, 1977), 61.

2. Henri Bergson, *Creative Evolution* (New York: The Modern Library, 1944), 53.

3. "The Eleatic School," in *The Presocratics,* ed. Philip Wheelwright (New York; The Odyssey Press, 1966), 97.

4. In this paper, the terms *Ethiopia* and *Ethiopians* refer to the mostly Orthodox Christian northern part of Ethiopia, previously known as "Habesha." However, even if this view does not originate in the southern part of Ethiopia, the deployment and dissemination of northern culture has made it representative of all of Ethiopia.

5. *Kebra Negast,* trans. Sergew Gelaw (Addis Ababa: Commercial Printing Press: 1994), 59.

6. Ibid., 60–61.

7. Kebede Mikael, *Yeqiné Azmara* (Addis Ababa: Birhanena Selam Printing Press, 1946), 97–99.

8. John Mbiti, *African Religions and Philosophy* (New York: Frederick A. Praeger, 1975), 17.

9. Mikael, 99.

10. *Kebra Negast,* 146.

11. Psalms 68:13.

12. *Kebra Negast,* 146.

13. Mikael, 35.

14. *Kebra Negast,* 149.

15. G. W. F. Hegel, *The Philosophy of History,* trans. J. Sibree (New York: Dover Publications, 1956), 103.

*Compiled early in the fourteenth century, the *Kebra Negast* is considered Ethiopia's most important literary work. Translated as the "Glory of the Kings," the book relates, among other things, the Solomonic descent of Ethiopian kings.

†Emperor Tewodros ruled Ethiopia from 1855 to 1868. Besides being the first emperor who seriously sought to unify and modernize Ethiopia, his other distinguishing feature was that his mother was so impoverished that she was selling *kosso,* which is a native herbal remedy against intestinal worms, mostly originating from